# የቨርጅኒያ የቅድመ-ትምህርት ቤት ተነሳሽነት (Virginia Preschool Initiative (VPI)
# የቅድመ-መዋዕለሕፃናት በምዝገባ ላይ ምልከታ-ማድረጊያ ዝርዝር (Checklist)

**ምዝገባው የሚካሄደው በቀጠሮ-ብቻ ነው**
**ከሰኞ – አርብ ከ9:00 a.m. እስከ 1:00 p.m. ድረስ**
**ወላጅ/አሳዳጊ፤ በስልክ የሚደረገ የምርመራ-ምልከታን (screening) ለማድረግ፣ ቀጠሮውን**
**በ: https://acpsvpi.setmore.com ላይ በመንብኘት፤ የጊዜ-ሰሌዳ መያዝ-አለባቸው።**
በስልካችሁ ቀጠሮ-ለመያዝ፣ ይህን 'ኪው-አር ኮድ/QR Code' - በስልካችሁ ካሜራ ስካን (Scan) አድርጉ።

**በምዝገባው-ሂደት ወቅት ላይ፤ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ - የሚከተሉትን ሁሉንም ሰነዶች ማቅረብ አለባቸው።**

## የምዝገባ ቅፆች:

- ☐ በመኖሪያ ቤት ውስጥ በሚነገር ቋንቋ – የዳሰሳ ጥናት
- ☐ የተማሪ የምዝገባ ቅጽ
- ☐ የነዋሪነት ማረጋገጫ እና የተመዘገቡበት ቅጽ
- ☐ የተማሪ የጤና መረጃ ቅጽ
- ☐ የቨርጂንያ ኮመንዌልዝ (Commonwealth of Virginia)፣ የትምህርት ቤት መግቢያ - የጤና ቅጽ
- ☐ የተማሪ-ወላጅ - የዳሰሳ-ጥናት
- ☐ የACPS የፊርማ ቅጽ

ይህንን ድህረ ገጽ (link) በመጠቀም ቅጾችን መኑላት ይችላሉ: www.acps.k12.va.us/Page/3073

## መታወቂያ (Identification):

- ☐ ኦሪጂናል የልደት ሰርተፊኬት/Original Birth Certificate ወይም ማረጋገጫ የተደረገበት/certified፣ የትውልድ ሰርተፊኬት (ልጁ፣ በሴፕቴምበር (September) 30 ቀን አራት-ዓመት ዕድሜ ሊኖረው ይገባል)
- ☐ ኦሪጅናል የወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ መታወቂያ (ID)፤ (ልጁን የሚያስመዘግበው አዋቂ-ሰው፣ ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ መሆኑን ማረጋገጫ) በልደት የምስክር ወረቀቱ ላይ ያለው ሥም፣ ወላጅ/አሳዳጊው ካቀረበው ፎተግራፍ ካለበት መታወቂያ (ID) ጋር፣ ወይም ከፍርድ ቤት ከተሰጠው ሕጋዊ አሳዳጊነት ሰነድ ጋር አንድ-ዓይነት ሆኖ መዛመድ አለበት።

## የሕክምና (Medical) ሰነዶች:

- ☐ **የአካላዊ ምርመራ (Physical Examination) ሪፖርት** የስቴቱ ሕግ (Ref. Code of Virginia § 22.1-270) በሚጠይቀው መሠረት፣ በአሜሪካ አገር ውስጥ ልጅዎ በሕዝብ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በቅድመ-ትምህርት ቤት ውስጥ ከመግባቱ በፊት፤ ሁሉን ያካተተ የሙሉ አካል ምርመራ (comprehensive physical examination) ማድረግ አስፈላጊ የሆነ መስፈርት ነው። ሙሉ-አካላዊ ምርመራው (physical examination) ወደ ቅድመ-ትምህርት ቤት ከመግቢያው-ቀን በፊት፣ በአንድ ዓመት ውስጥ የተደረገ መሆን አለበት።
- ☐ **በአሜሪካ አገር ውስጥ የተደረገ፤ በሽታው እንደሌለ (Negative የሆነ) የሳንባ ነቀርሳ ሲጋት ግምገማ (Tuberculosis Risk Assessment)፣ የPPD ቱበርኪውሊን የቆዳ ላይ ምርመራ (Tuberculin Skin Test) ወይም በሽታው እንደሌለ (Negative የሆነ) የደረት-ኤክስሬ (Chest X-Ray)፣** ልጁ - ወደ ትምህርት ቤት ከሚገባበት የመጀመሪያ ቀን በፊት፣ በ12 ወራቶች ውስጥ ተደርጎ-የተጠናቀቀበትን መረጃ።
- ☐ **የክትባት መዝገቦች/Immunization Records (በሰነዱ ላይ፤ ክትባቱ የተሰጠበትን - ወር፣ ቀን እና ዓመት ምህረትን፣ የሚያሳይ)**

- **(4 ዶዞች/doses) - የ'Diphtheria, Tetanus, Pertussis (Dtap, DTP or Tdap)'** ቢያንስ - አራት ዶዞች (four doses)፤ አንደኛው የሚሰጥ-ክትባት (dose) በአራተኛው የልደት-ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ የተሰጠ።
- **(3 ዶዞች/doses) የ'POLIO (OPV or IPV)'** ቢያንስ ሦስት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት/dosesን፤ አንደኛው ክትባት፣ በአራተኛው የልደት-በዓት ላይ ወይም ከዚያ በኋላ የተሰጠ ክትባት።
- **(3 ዶዞች/doses) የ'HEPATITIS B'** ሦስት ተከታታይ የሄፒታይተስ ቢ (Hepatitis B) ክትባትን ተከትበው ማጠናቀቅ፣ ለሁሉም ልጆች አስፈላጊ መስፈርት ነው።
- **(2 ዶዞች/doses) የ'Hepatitis A (HAV) Vaccine'** ቢያንስ ሁለት ዶዞችን (two doses)፣ ለሄፒታይተስ ኤ (Hepatitis A) ክትባትን ማግኘት። የመጀመሪያው-ክትባት መሰጠት ያለበት፣ በ12 ወራት ዕድሜ ላይ፣ ወይም ከዚያ በላይ ሲሆኑ ነው።
- **(1 ዶዝ/dose) የ'Measles, Mumps, & Rubella (MMR)'** ቢያንስ አንድ-ጊዜ የሚሰጥ ክትባት/doseን፤ ሌላ አንድ ክትባት/doseን በአራተኛው የልደት-በዓት ላይ ወይም ከዚያ በኋላ የተሰጠ ክትባት።
- **(1 ዶዝ/dose) የ'Varicella (Chicken Pox)'** ቢያንስ አንድ-ጊዜ የሚሰጥ ክትባት/doseን፤ ሌላ ተጨማሪ አንድ ክትባት/doseን በአራተኛው የልደት-በዓት ላይ ወይም ከዚያ በኋላ የተሰጠው።
- **(1 ዶዝ/dose) የ'Haemophilus Influenzae (Hib)'** ዕድሜያቸው በ15 እና 60 ወራት ውስጥ የሆኑ ያልተከተቡ ልጆች፤ አንድ-ጊዜ ብቻ የሚወጉት ክትባት ብቻ የሚያስፈልጋቸው ይሆናል።
- **(1 ዶዝ/dose) የ'Pneumococcal Vaccine (PCV)'** ይህ ክትባት የሚያስፈልገው ከ60 ወራት ዕድሜ በታች ለሆኑ ልጆች ብቻ ነው። የመጀመሪያ ሊሰጥ የተፈለገው የኑሞካኩል (pneumococcal) የተጣመረ ክትባት መሰጠት አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ዕድሜ መሠረት-አድርጎ፣ ከአንድ እስከ አራት ጊዜ የሚሠጥ ይሆናል።

ክትባቶች ያልሰሩ-ከሆነ - ይህ አስፈላጊ ነው: አዲስ-የወጡ ክትባቶች ተሰጥቶ ከነበረ፣ የሙያ ፈቃድ ያለው የጤና እንክብካቤ ሰጪ በመቀጠል የሚሰጡ ተጨማሪ ክትባቶችን - የሚሰጥበትን የጊዜ-ሰሌዳ ቀን የሚያሳይ፣ የፅሁፍ ማሳሰቢያ መስጠት አለበት። በተጨማሪ፣ ትክክለኛ-የሆነ በክትባቶች መካከል ሊኖር የሚገባ የጊዜ ክፍተትን መከተል ያስፈልጋል። ተጨማሪ የሆነ ክትባት ከተወሰደ፤ ወደ ትምህርት ቤቱ ነርስ የሚቀርብ የፅሁፍ ሰነድ ያስፈልጋል። በተሰጠው ቀን ላይ፣ ክትባቶቻቸውን (immunizations) ማጠናቀቅ ያልቻሉ ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት ውስጥ የማይካተቱ ይሆናል።

**በገጹ ግልባጭ-በኩል ያለውን ይመልከቱ **

# የቨርጅኒያ የቅድመ-ትምህርት ቤት ተነሳሽነት (Virginia Preschool Initiative (VPI)
# የቅድመ-መዋዕለሕፃናት በምዝገባ ላይ ምልከታ-ማድረጊያ ዝርዝር (Checklist)

## የገቢ (Income) ማረጋገጫ:

እባክዎን የሚከተለውን የቅርብ-ጊዜ ሰነዶችን ያቅርቡ (የሚመለከተዎትን በሙሉ ይምረጡ):

- ☐ የገቢ ታክስ (Income Tax) ቅጽ/Form 1040
- ☐ W-2
- ☐ ሁለት (2)፣ በቅርብ ጊዜ ደሞዝ የተከፈለበት (pay stubs) - (በ30 ቀናት ውስጥ ያለ)
- ☐ የሥራ-አጥነት (Unemployment ) እና የማካካሻ ክፍያ የሚያገኝ ሠራተኛ (workers' compensations)
- ☐ ማሟያ የደህንነት ገቢ (Supplemental Security Income (SSI)
- ☐ ጊዜያዊ የችግረኛ ቤተሰቦች ድጋፍ (Temporary Assistance for Needy Families (TANF)
- ☐ ተጨማሪ ተመጣጣኝ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (Supplement Nutrition Assistance Program (SNAP)
- ☐ የ'ሜዲኬድ/Medicaid' ደብዳቤ
- ☐ ኖተራይዝድ የሆነ (Notarized)፣ የገቢ (Income) ማረጋገጫ ቅጽ
- ☐ ኖረራይዝ የሆነ (Notarized) የሥራ-አጥነት ማረጋገጫ (Unemployment Verification) ቅጽ
- ☐ ከትምህርት እገዛ የሚገኝ ገቢ (Income)
- ☐ አልሞኒ (Alimony) ወይም የልጅ እርዳታ
- ☐ ከእርስት እና ከአደራ የተገኘ ገቢ (Income)
- ☐ የኪራይ እና የባለቤትነት መብት (royalties)
- ☐ የጡረታ-ዓበል ወይም ከስራ በመሰናበት የተገኘ ገቢ
- ☐ የቀድሞ የውትድርና አባል ከመሆን፣ የተገኘ የጥቅማ-ጥቅም ክፍያ
- ☐ ከማደጎ አገልግሎት ተመላሽ ክፍያ (Reimbursement)
- ☐ ከቤተሰቡ ውጪ የመጣ የገንዘብ እርዳታ

## የነዋሪነት ማረጋገጫ:

የሚያስመዘግበው-አዋቂ ሰው፣ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ያስፈልገዋል: ሁሉም ሰነዶች፣ ዋናው ኦሪጅናል (original) የሆኑ-መቅረብ አለበት (በአሁኑ-ወቅት-ባለፉት 60 ቀናቶች ውስጥ የሆነ) እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ፣ የወላጅን/ሕጋዊ አሳዳጊን ሥም እና የአሌክሳንድሪያ ከተማ አድራሻን የሚያሳይ መሆን አለበት።

### ☐ በምድብ (Category) A – ውስጥ፣ አንድ (1) ሰነድን መመረጥ-አለበት:

- **ሙሉ የሊዝ ወይም የኪራይ ስምምነት:** ኦሪጅናሉ ሊዝ፣ ወቅቱን-የጠበቀ (ጊዜው ያላለቀበት) መሆን ያለበት እና፤ ቀኖችን፣ ስሞችን እና የንብረቱን አድራሻ የሆነውን - ተማሪውን የሚያስመዘግበውን ወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊውን አካትቶ የያዘ መሆን አለበት። ሊዙ፤ ከቤቱ-ባለቤት በግል የተሰጠ ስምምነት ከሆነ፣ ሊዙ ኖተራይዝ (notarize) መደረግ አለበት።
  - የሊዝ ስምምነታችሁ ጊዜ-ያለፈበት (expired ከሆነ) እና ሊታደስ የማይችል ከሆነ፤ <u>ሁለቱንም</u> - ሙሉ ጊዜስ-ያለፈበትን የሊዝ ስምምነት (full expired lease agreement) <u>እና</u>፣ የአሁኑን (በ60 ቀናቶች ውስጥ ያለውን) ከሊዝ ቢሮው የተሰጠ - *በአሁኑ ጊዜ ሊዛችሁ ወር-ከወር (month to month) በሆነ አሰራር ላይ እንዳለ የሚገልጽ*፣ የተፈረመበትን ደብዳቤ ማስገባት <u>አለባችሁ</u>። ደብዳቤው፣ በድርጅቱ የደብዳቤ-ማፊያ ወረቀት (letterhead) ላይ የተፈረመ ወይም ኖተራይዝ የተደረገ፤ ቀን፣ የወላጅ/አሳዳጊ ስም፣ እና አድራሻን ጨምሮ የያዘ መሆን አለበት።
- **ሞርጌጅ (Mortgage):** ነዋሪው፤ በአበዳሪው - የተዘጋጀውን የሞርጌጅ መከፈያን (ቀን፣ የአሌክሳንድርያ አድራሻ፣ እና የአበዳሪ ስም ያካተተ) በ60 ቀናት የምዝገባ ጊዜ ወይም የመጀመሪያ የሞርጌጅ ኮንትራትን በአሁኑ-ጊዜ ካለው የንብረት ባለቤትነት ታክስ ቅጂ ጋር ሊያቀርቡ ይገባል።
- **ዲድ (Deed):** የንብረቱ ዲድ (property deed)፣ ከባለቤቱ የግል የንብረቱ ታክስ ቅጂ (copy) አብሮ-ተያይዞ መቅረብ አለበት።

### ☐ በምድብ (Category) B - ውስጥ፣ ሁለት (2) ሰነዶችን-መመረጥ አለባቸው:

- የዩቲሊቲ የክፍያ-መጠየቂያ/Utility bill (ውሃ፣ ጋዝ፣ ኤሌክተርክ፣ ኢንተርኔት፣ ኬብል እና/ወይም የቤት-ውስጥ ስልክ-የክፍያ መጠየቂያ) የክፍያ-መጠየቂያው (bill)፣ ባለፉት <u>60 ቀናት</u> ውስጥ የተከፈለ መሆን አለበት። ሁሉም የዩቲሊቲ ክፍያዎች፣ ከሊዝ ኮንትራታችሁ ጋር አብሮ ከሆነ እና ምንም የክፍያ-መጠየቂያዎች (bills) ከሌሏችሁ፤ እባካችሁን፣ ከንብረቱ ተቆጣጣሪ (property manager)፣ በድርጅቱ የደብዳቤ-ማፊያ (letterhead) ላይ የተፃፈ፣ ውሃ፣ ጋዝ፣ ፍሳሽ፣ እና ኤሌክትሪክ ያሉት ሁሉ በወሃዊ ኪራዩ ውስጥ የተካተተ መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ አቅርቡ።
- ከመንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ወደ አድራሻዎ የተላከ ደብዳቤ (ከ'SNAP'፣ TANIF፣ ሜዲኬድ/Medicaid፣ HUD, ARHA, IRS, ወዘተ...)
- የቅርብ ጊዜ የደሞዝ ክፍያ (pay stub) - (የአሌክሳንድሪያ አድራሻን እና የቨርጅኒያ የታክስ ተቀናሽ (Virginia tax withholding) የሚያሳይ)
- 2 ተከታታይ-የሆኑ የባንክ ስቴትመንቶች (bank statements)፣ ወደ አሌክሳንድርያ ከተማ አድራሻ መላኩን የሚያሳይ
- የቅርብ ጊዜ የፌደራል/የስቴት የገቢ ታክስ ተመላሽ (income tax return) - የአሌክሳንድሪያ አድራሻ ያለበት
- የቅርብ-ጊዜ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ፤ የአሌክሳንድሪያ አድራሻ ያለበት
- ለአሌክሳንድሪያ ከተማ አዲስ (ከ30 ቀናት ያነሰ ጊዜ)፣ ቤተሰቡ አዲስ የመጡ መሆናቸውን የሚያሳይ። ከምዝገባው በኋላ - በ30 ቀናት ውስጥ ያበቃል።

### ☐ ምድብ (Category) C:

- የመኖሪያ-ቤት እጦት (Lack of Housing)
- DSS/የማደጎ እንክብካቤ አገልግሎቶች (Foster Care Services)

### ☐ በመጋራት-በሚኖሩበት መኖሪያ-ቤት ውስጥ፤ ነዋሪዎች:

- ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ - ከሌላ ሰው ጋር እየኖሩ ከሆነ (እና ሊዝ/lease፣ ዲድ/deed፣ ወይም ሞርጌጅ/mortgage - በወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊው ስም ካልሆነ)፤ ኖተራዝይ/notarized የተደረገ የShared Housing Form A/B (PDF)ን ማጠናቀቅ-<u>ያለባችሁ</u> እና፣ አብራችሁ የምትኖሩት ሰው ያለውን የሊዝ/lease፣ ዲድ/deed፣ ወይም ሞርጌጅ/mortgage ኦሪጂናል (original) ቅጂውን ማያያዝ-አለባችሁ። በተጨማሪም፣ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት (በወላጅ/ሕጋዊ አሳዳጊ ሥም የሚገኝ) - ሁለት ደጋፊ-የሆኑ ሰነዶችን (supporting documents) ማቅረብ ያስፈልጋቸዋል።